www.ginbot7.org
የግንቦት 7 ድምጽ
የግንቦት 7፣ የፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

ቀን፤ሐምሌ 10 2000 ዓ.ም የግንቦት7 ድምጽ ቁጥር 9

## ኢ.ህአዴግ የዘረፈው ብር እየተድበሰበሰ ነው፡፡

“ባንክ መዝረፍ የተካኑበት ነው” ( የአዲስ አበባ ነዋሪዎች)

“ የኦዲት ሪፖርቱ የኢትዮጵያን ስም የሚያጠፋ ነው፡፡” (ሽፈራው ጃርሶ)

የፌዴራል ምክትል ዋና ኦዲተሩ አቶ አሰፋ ደስታ፤ ኢ.ህአዴግ ራሱ ካወጣው መመሪያና ህግ ውጭ 3 ቢሊዮን 295 ሚሊዮን 400 ሺህ ብር በብድር መልክ ከባንክ መውሰዱን ባጋለጡ ማግስት፣ አቶ መለስ ያቋቋሙት አጣሪ ኮሚቴ፤ የኦዲት ሪፖርቱን ውድቅ አድርጎ ሌላ ሪፖርት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ የተላለፈለትን ትዕዛዛ አዘል ምክር ለማስፈፀም ደፋ ቀና እያለ መሆኑን ምንጮቻችን ገለፁ።
ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተሉ ያሉ ታማኝ ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ባደረሱን መረጃ መሰረት፤ በገለልተኛነት ስም አቶ መለስ ያቀረቧቸው አምስት የአጣሪ ኮሚቴ አባሎች፤ ቀንደኛ የኢ.ህአዴግ ደጋፊዎች በመሆናቸው፤ በኢ.ህአዴግ በኩል ስህተት እንዳልተፈፀመ የሚያሳይ ሪፖርት በፍጥነት ሰርተው ይፋ በማድረግ ገዥውን መንግስት በተለይ ከዓለም ባንክ ወቀሳ የሚታደግ ሪፖርት ሰርተው ያቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የመለስ አገዛዝ ለህሊናቸውና ለሙያቸው ቀናኢ የሆኑ ግለሰቦች በአገዛዙ ላይ የሚያቀርቡዋቸውን በጥናትና በመረጃ የተደገፉ የወንጀል ማስረጃዎች ማጣጣል ልማዱ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ጉዳይ የቅርብ ግዜ ትውስታው የሆነው ሃገሬ "አሁን የቆመው ኮሚሽን ከእዚህ ቀደም በግንቦት 97 ምርጫ ወያኔ ኢ.ህአዴግ የፈጸመውን የግድያ ወንጀል ለማጣራት ተቋዋቁሞ የነበረውን ኮሚሽን ያቀረበውን ሃቀኛ ሪፖርት ለወያኔ በሚስማማ መንገድ ቀይሮ ለማቅረብ የተቋዋቋዋመውን በገዥው ስርአት ካድሬዎች የተሞላውን ተለጣፊ ኮሚሽን እንድናስታውስ ያደርገናል" እያለ ነው፡፡

በመሆኑም ሪፖርቱ በቀረበበት ዕለት “በአሰራራችን መሰረት በበጀት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይታያል” ያሉት አቶ ሽፈራው፤ በቀጣዩ ቀን ቃላቸውን በማጠፍ ፦"መታየት ያለበት በገለልተኛ ኮሚቴ ነው” በማለት የጌታቸውን የመለስን ሀሳብ አስተጋብተዋል፡፡

ምክትል ዋና ኦዲተሩ ማንንም ሳይፈሩ ያቀረቡት ሙያዊ ሪፖርት አንዳችም ስህተት እንደሌለበት በበርካታ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እየተመሰከረ ያለ ቢሆንም፤ ሲሳሳቱም ጭምር ጭብጨባ እንጅ ተግሳፅ ያልለመዱት ኢ.ህአዴጋውያን፤ በምክትል ዋና ኦዲተሩ በአቶ አሰፋ ላይ ቁጣቸውን ሲገልፁ ሰንብተዋል።

በተለየ መልኩ አቶ መለስ፣ የብሄራዊ ባንክ ገዥ አቶ ተክለወልድ አጥናፉ እና የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ ሶፊያን አህመድ ዋና ኦዲተሩን ሲወርፏቸው ሰንብተዋል።

አቶ መለስ፤ በመንግሰታቸው አሰራር ሳይሆን በራሳቸው ፈቃድ ያቋቋሙት ኮሚቴ ግራ ያጋባቸው አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል "የማጣራት ጥያቄ ያቀረበው ኢ.ህአዴግ፣ ከተፈቀደለት በጀት በላይ የተጠቀመው ኢ.ህአዴግ፣ ገለልተኛ ኮሚቴ መልምሎ ያቀረበው ኢ.ህአዴግ” ሲሉ ተደምጠዋል።

በጉዳዩ ዙሪያ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፤ "የአገር ሀብት በአንድ ፓርቲ መዘረፍ የጀመረው ኢ.ህአዴግ ገና ስልጣን ላይ ሲወጣ ጀምሮ መሆኑን በማስታወስ፤ ’አሁንም በረሀብና በኑሮ ውድነት እየተሰቃየን ያለንበት ምክንያት አልጠፋንም” ብለዋል።